# ለአስም የመጀመሪያ እርዳታ የሚወሰዱ 4 እርምጃዎች



## 1

ሰውየው ወደላይ ቀጥ ብሎ መቀመጥ



## 2

ሰማያዊ/ግራጫ ቀለም ያለውን የትንፋሽ ማስታገሻ የተለያየ 4 ንፊቶች/ puffs ማድረግ

– መንፊያውን መወዝወዝ
– **1 ንፊት/puff** በመያዣ ጋን ውስጥ ማስቀመጥ
– ከመያዣ ጋን ውስጥ **4** ትንፋሾች መውሰድ

**4** ንፊቶች/puffs እስኪወሰድ ድረስ መደጋገም

አስተውሉ: መወዝወዝ፣ **1 ንፊት/puff**፣ **4** ትንፋሾች

ወይም 2 የተለያየ መጠን ያለውን የ Bricanyl አየር ወደ ውስጥ መሳቢያ (እድሜው 6 እና ከዚያ በላይ ለሆነ) ወይም የ Symbicort ወደ ውስጥ መሳቢያ (ከ12 ዓመት እድሜ በላይ ለሆነ) መስጠት




## 3

**4** ደቂቃዎች መቆየት

ምንም ለውጥ ከሌለ፤ ከዚህ በላይ እንዳለው ተጨማሪ የሰማያዊ/ግራጫ ቀለም ያለውን የትንፋሽ ማስታገሻ **4** የተለያየ ንፊቶችን/ **puffs** መስጠት

ወይም በተጨማሪ 1 መጠን ያለው የ Bricanyl ወይም የ Symbicort አየር ወደ ውስጥ መሳቢያ መስጠት




## 4

አሁንም ለውጥ ካልተገኘ ለአምቡላንስ በስልክ ሶስት ዜሮ (000) አድርጎ መደወል

ለድንገተኛ ችግር እርዳታ እስከሚደርስ በየ 4 ደቂቃዎች 4 የተለያየ ንፊቶች/puffs እየሰጡ መቆየት

ወይም 1 መጠን ያለው የ Bricanyl ወይም የ Symbicort በየ 4 ደቂቃዎች – በተጨማሪ እስከ 3 መጠን ያለው Symbicort

ለድንገተኛ ችግር እርዳታ ወዲያውኑ መደወል። በስልክ ሶስት ዜሮ (000) መደወል:

- ሰውየው የማይተነፍስ ከሆነ።
- የሰውየው አስም እየባሰበት ከመጣ፤ ወይም መሻሻል ካላሳየ።
- ሰውየው አስም ከተነሳበት እና የትንፋሽ ማስታገሻ ከሌለ።
- አስም ስለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑ።
- ሰውየው በሆነ ምክንያት የሰውነት መቆጣት አለርጂ/anaphylaxis ካለበት – የራሳቸውን አለርጂ/ Anaphylaxis የድርጊት መመሪያ መከተል፤ ከዚያም ለአስም የመጀመሪያ እርዳታ መስጠት። እንኳን ሰውየው አስም ባይኖርበትም ሰማያዊ/ግራጫ ቀለም ያለው የትንፋሽ ማስታገሻ መድሃኒት መውሰዱ ጉዳት እንደሌለው ነው።

ከዚህ የአበባ ብናኝ ያለበት ወራት እራስዎን ይጠብቁ።

ከአስምና አለርጂ በተዛመዱ ጉዳዮች ላይ መቆጣጠር።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት በድረገጽ betterhealth.vic.gov.au ላይ ማየት ወይም በስልክ 1800 ASTHMA (1800 278 462) መደወል።

በቪክቶሪያ መንግሥት የተፈቀደና የታተመ፤ 1 Treasury Place, Melbourne (1708026)
© በቪክቶሪያ አስተዳደር ግዛት (Department of Health and Human Services).
ከድርጅት ዓርማ በቀር፤ በCC BY International 4.0 መሰረት ፈቃድ ያገኘ።

ASTHMA AUSTRALIA

VICTORIA State Government